## ባለቤትዎ ወይም ወዳጅዎ

- በቡጢ፣ በጥፊ፣ በቡጥጫ ወይም በርግጫ ይመታዎታል?
- ልጆችዎን፣ የቤት እንስሳዎችንስ - ውሻ፣ ድመትዎን ይመታል?
- እንደሚገድሉት ወይም እንደሚጎዳዎት ያስፈራሮታል?
- የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያለውዴታዎ እንዲያደርጉ ያስገድዶታል?
- ለኢሚግሬሽን ቢሮ ነግሬ ወደ አገር ቤት እንዲመለሱ አደርጋለሁ በማለት ያስፈራሮታል?
- ልጆችሽን እወስድብሻለሁ በማለት ያስፈራሮታል?
- ልጆችሽን እወስድብሻለሁ በማለት በዛቻ ጭምር ያስፈራሮታል?
- ከማን ጋር እንደሚገናኙና ከማን ጋር እንደሚያሳልፉ ይቆጣጠራሉ?
- ገንዘብ እንዳይነኩ ይቆጣጠሮታል? ገንዘቦን ይወስድቦታል? ያጠፉትን ገንዘብ እያንዳንዷን ሳንቲም እንዴት እንዳጠፉ እንዲገልጡ ያስገድዶታል?
- ሥራ እንዳይሰሩ ይከለክሎታል፣ እንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲማሩ አይፈቅዱም?
- የኢምግሬሽን ወረቀቶችን ፋይል አላደርግም ይላሉ፣ ይዘው አልሰጥም ይላሉ?

## የቤት ውስጥ ጥቃት /በደል ምን ማለት ነው?

## (Domestic Violence)

የቤት ውስጥ ጥቃት ማለት በቅርብ በሚተዋወቁ ሰዎች፡- እንደባልና ሚስት፣ ወዳጆች፣ ዘመዳሞች፣ በወላጆችና በልጆች መካከል የሚከሰት የቤት ውስጥ ጥቃት ማለት ነው።

የቤት ውስጥ ጭቆና በቤት ውስጥና እንዲሁም በሌላ ሥፍራ ሊከሰት ይችላል እንዲሁም ከላይ የጠቀስናቸው አባሎች አብረው ሲኖሩ፣ ሲለያዩ (Separation)፣ ሲፋቱ ሊከሰት ይችላል።

የቤት ውስጥ ጥቃት በቅርብ ወዳጆች ወይም በቤተሰብ ግንኙነት መካከል የሚገለጥ የአንድ ሰው አምባገነን የሆነ ባሕሪ ነው። ይኼ ባሕሪ ጨቋኝ የሚሰኝበት ምክንያት እንዲህ ያለበት ሌላውን ሰው በማስፈራራትና በማስገደድ ፀባዩን እንዲቀይር በማድረጉ ነው።

ብዙውን ጊዜ ይህ ጥቃት በአካል ላይ ጉዳት በማድረስ የሚገለጥ ቢሆንም በማስፈራራት፣ አንድ ሰው ከሌላ ሰዎች እንዲነጠል በማድረግ፣ በዛቻ በማስጨነቅ፣ ሞራል በመንካት፣ አስገድዶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ በማድረግ እንዲሁም እርሶን ወይም ልጆችዎን ወደ አገር እንዲመለሱ አደርጋለሁ በማለት በዛቻና በማስፈራራት ሊፈፀም ይችላል::

በቤት ውስጥ ጭቆና ካለቦት ብቻዎትን አይደለም:: ምንም እንኳ የቤት ውስጥ ጭቆና የሚከሰተው በድብቅ ቢሆንም በጣም የተለመደ ነገርና በብዙዎች ዘንድ የሚደረግ ምናልባትም እርሶ የሚያውቋቸውን ብዙ ሰዎች የሚነካ ተፅዕኖ የሚያደርግባቸው ነገር ይሆናል::

ይህ ጽሑፍ የቤት ውስጥ ጥቃት ተቃዋሚ ድርጅት በኢምግሬሽን ቢሮ ወደ አገር ቤት እንዲመለሱ ሳይደረጉ እንዴት አድርገው የቤት ውስጥ ጥቃትን መከላከል እንደሚችሉ ይገልፃል::

በአሜሪካ የሚኖሩ የተጠቁ /የተጎዱ/ ሴቶች ሊያገኙት የሚችሉት እርዳታ (Help All Battered Women can Keeled) በአሜሪካ ውስጥ ሕጋዊነት ባይኖሮት ወይም ሕጋዊ የነዋሪነት ፍቃድ ወረቀት የሚያገኙበት መንገድ አጥቂው የሥራ ፍቃድ ጋር የተያያዘ ቢሆን እንኳ በሚደርስበት ጥቃት ምክንያት የሚከተሉትን ጥቅም ማግኘት ይችላሉ::

☐ ከመጠለያ ሰጪዎችና ከሌሎች የቤት ውስጥ ጥቃት ተቃዋሚ ድርጅቶች አገልግሎትን /እርዳታን

☐ የዜግነት ጥበቃ ትዕዛት ከፍርድ ቤት

☐ ልጆችን የማሳደግ መብትና ድጋፍ

☐ የፖሊስ ድጋፍ አገልግሎት

☐ የድንገተኛ ሕክምና ድጋፍ

3 ☐ የተጨቆኘ /የተጠቁ ሴት ባለቤት ዌቨር /ነፃ ዕድል/ ማመልከት

4 ☐ የወንጀሉ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የሚፈቀድ ቪዛ "ህ" ቪዛ በመባል ለሚታወቅ ቪዛ ማመልከት

5 ☐ በሆቴ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ጥገኝነት ፋይል መክፈት

## የዚህ ዓይነት ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎችን

ወደ አሜሪካ የመጡት በግዳጅ፣ በመታለልና መበደል ከሆነና ለዚህ ነገር ሰለባ ሆኛለሁ ብለው የሚያምኑ ከሆነ T Visa ለሚባለው ቪዛ ያሟሉ ይሆናል። ለ "T" Visa መስፈርት ለማሟላት እንዲሆን ሲባል ማጓጓዝ Trafficking የሚለው ቃል እንዲህ ተተርጉሟል።

ማዘዋወር Trafficking ማለት አንድን ሰው ለግብረሥጋ ግንኙነት መፈፀሚያ በግዳጅ፣ በማታለልና በማጭበርበር በገንዘብ ልውውጥ ለሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚደረግ ማጓጓዝ። እንዲሁም እንዲህ ያለውን ነገር እንዲፈፅም የሚደረገው ሰው 18 ዓመት ያልደረሰ ሲሆን እንዲሁም የሚያዘዋውሩትን ሰዎች ምልመላው ከቦታ ወደ ቦታ ማዘዋወሩ፣ ለጉልበት ሥራ አገልግሎት በግዳጅ፣ በኃይል በመጠቀም፣ በማጭበርበር ባሰቦት ባልተስማማበት ሁኔታ በባለእዳነት የበታች በማድረግ በባርነት ወደራስ ማስጠጋት /ለራስ መውሰድና ለዚሁ ጥቅምና አገልግሎት ለሌላ ሰው ሓሳልፎ መስጠት ማለት ነው።

ለ T Visa ለማግኘት የሚከተሉትን 4 መስፈርቶች ማሟላት አለቦት

☐ በግዳጅ ወይም በጭከና የተደረገ የመጓጓዝ ሰለባ መሆን አለቦት

☐ አሁን በአሜሪካ ውስጥ ፣ በአሜሪካ ሳሞአ (American Samoa), (Common wealth of the Northern Marina Islands) ወይም አሜሪካ መግቢያ ወደብ /እውርፕላን ማረፊያ በአካል መሆን አለቦት

☐ አጥቂው በእጁ የሚገኙትን መሣሪያዎችና ንብረት ሁሉ እንዲሁም ፍርድ ቤት የሚፈርድበትን ንብረት ሁሉ እንዲያስረክብ ይጠይቃል።
ሕጋዊ የመኖሪያ ፍቃድ ባይኖሮት ነገር ግን ባለቤትዎ ቢኖረው የልጆቻችሁን ጊዜያዊ ሞግዚትነት መብት እንዲሰጠ፤ ይህ ሞግዚትነት የተሰጠት የጥበቃ ትዛዝ እስከሚያገለግልበት ድረስ ያገለግሎታል። ቋሚ ሞግዚትነት ለማግኘት ግን ብዙዎቹ ክፍለ ሀገሮች (States) እንደሚያደርጉት ፍርድ ቤት (Family Court) በመሄድ ፋይል መክፈት አለቦት

☐ ትዕዛዙ በሥራ ላይ እያለ የልጆች ማሳደጊያ ድጎማና እንዲሁም የሕክምና አገልግሎት ለእርሶና ለልጆች መጠየቅ ይችላሉ።

☐ አጥቂው የልጆቹን ፓስፖርት እንዲያስረክቦት
ለበዳዩ/ጨዳጅኑ የሚፈቅድላቸው የልጆቹን መጎብኛ ጊዜ ሦስተ ሰው የጨመረ እንዲሆንና እርሶን፣ ልጆቹዎን ወይም ተጨማሪውን ሰው አደጋ ላይ የማይጥል እንዲሆን። በዳዩ /ጨዳጁ የሚሰጠው ልጆቹን የመጎብኛ ጊዜ ሰዓትና ቀን መለወጥ የማይችሉ ቋሚ ትዕዛዝ እንዲሰጥ።

☐ በዳዩ/ጨዳጁ በጠብ ጊዜ ለሚደርሱ የህክምና ወጪ፣ የንብረት ጥፋት፣ ወጪውን እንዲከፍሉ

☐ ፖሊስ የጥበቃ /ዕገዳ ትዕዛዙን ተፈፃሚ ለማድርግ እንዲረዳዎትና በመኖሪያ ስፈር የቅርብ ጥበቃ እንዲያደርግሎት

☐ በሴቶች ላይ የሚደረግን የቤት ውስጥ ጥቃትን በሚቃወም ደንብ መሠረት (VAWA) በተበዳዮች ለሚከፈተው የቫዋ (VAWA) ቪዛዎት እንዲሁም ሌላ ከቤት ውስጥ ጭቆናን የሚቃወም የኢምግሬሽን እርዳታ ማመልከቻዎ ተቀባይነትን እንዲያገኝ የሚረዳዎት መረጃዎችን በዳዩ/አጥቂዎት እንዲያስረክቦት ይጠይቁ።

